005

# የ1976 ዓ.ም. ብሔራዊ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ

## የተቆጣጣሪዎች መመሪያ

የአስታታስቲክስ ጠቅላይ ጽ/ቤት
ህዳር 1976 ዓ.ም.

# ማውጫ


| ተ.ቁ | አርዕስት | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ............................ | 1 |
| 2 | የተቆጣጣሪዎች አጠቃላይ መመሪያዎች................ | 1 |
| 3 | የተቆጣጣሪዎች ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት.......... | 3 |
| | ሀ. ከቆጠራው በፊት የሚከናወኑ ተግባሮች.............. | 3 |
| | ለ. በቆጠራው ጊዜ የሚከናወኑ ተግባሮች............... | 12 |
| | ሐ. ቆጠራው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚከናወኑ ተግባሮች...... | 21 |
| 4 | በቆጣሪዎች ላይ ሊታዩ የሚችሉ ጉልህ ድክመቶችና መወሰድ የሚኖርባቸው አርምጃዎች...................... | 25 |

## መግቢያ፣

የቆጠራው ዓላማዎችና ግቦች በቆጠሪዎች መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩ ቢሆን ይህንን በመመልከት ብቻ የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ በአገሪቱ ለሚካሄዱ የልማትና ሌሎች እንቅስቃሴዎች ከፍተኛና መሠረታዊ ጥቅም ያለው መሆኑ በቀላሉ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በ________ ቀን 1976 ዓ.ም. የሚካሄደው የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ በአገሪቱ የመጀመሪያው እንደመሆኑ መጠን የዚህም ቆጠራ ዓይነት በየአሥር ዓመት ይካሄዳል ተብሎ ስለሚገመት በጥንቃቄ መካሄድ አለበት፡፡

ተቆጣጣሪዎች ቆጠሪዎችን በቀጥታ እየተቆጣጠሩ፣ እየተከታተሉና እየረዱ የመረጃ ስብሰባውን ሥራ የሚያስፈጽሙ ስለሆኑ በቆጠራው መረጃዎች በትክክልና በተሟላ ሁኔታ እንዲሰበሰቡ ያደርጋሉ፡፡ ስለሆነም የካርታ አጠቃቀም፣ የምዝገባ፣ የቆጠሪዎች፣ የተቆጣጣሪዎችና ሌሎች መመሪያዎችን ጠንቅቀው እስኪያውቁ ድረስ በከፍተኛ ደረጃ በማጥናትና በመረዳት እንዲሁም አስፈላጊ የሒሳብ ዝግጅት በማድረግ ለሥራው መሠለፍ አለባቸው፡፡ ይህም ማለት በፍጹም ማስተዋል፣ በቅልጥፍናና ባለመሰልቸት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ የቆጠራው ሥራ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተሳካ እንዲሆን ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ስለዚህ የተቆጣጣሪነት ሥራ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ ለዚህ ሥራ የተመለመሉ ግለሰቦች ባላቸው ልምድ፣ ችሎታ፣ ብስለትና ንቃት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ይወጣሉ ተብለው የታመነባቸው ናቸው፡፡

በዚህ መመሪያ ውስጥ "የተቆጣጣሪዎች አጠቃላይ መመሪያዎች" የተዘረዘሩ ከመሆናቸውም በላይ ተቆጣጣሪዎች የቆጠራውን የመረጃዎች ስብሰባ ሥራ በተመደበው ጊዜ ውስጥ በትክክል ለማካሄድ እንዲችሉ. በየደረጃው ማከናወን ያለባቸውን ተግባርና ኃላፊነት "ከዋናው ቆጠራ በፊት የሚከናወኑ ተግባራት"፣ "በዋና ቆጠራ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት"፣ ዋናው ቆጠራ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራት" በሚል ዓበይት ርዕሶች. ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ በመጨረሻም ተቆጣጣሪዎች ኃላፊነታቸውን የማይወጡ ቆጠሪዎች ለመለየትና ለመቆጣጠር ይረዳቸው ዘንድ "በቆጠሪዎች ላይ ሊታዩ የሚችሉ ጉልሕ ድክመቶችና መወሰድ የሚኖርባቸው እርምጃዎች" በሚል ርዕስ ሥር አንዳንድ ጠቃሚ ጥቆማዎች ተደርገዋል፡፡

## የተቆጣጣሪ. አጠቃላይ መመሪያዎች፣

እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ በተመደበበት የመቆጣጠሪያ ቦታ በሥሩ የተመደቡትን ቆጠሪዎች በማስተባበር፣ በመቆጣጠር፣ በመከታተልና በመርዳት በትክክል እንዲከናወን የማ

ዱረግ ኃላፊነት ስለለበት ይህንን ለመወጣት እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ የሚከተሉትን
መፈጸም ይኖርበታል::

1. በተቆጣጣሪዎችና በቆጣሪዎች ሥልጠና ይሳተፋሉ:: እንዲሁም በቆጣሪዎች ሥል
ጠና አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል::

2. ኃላፊነትን በሚገባ ለመወጣት እንዲቻል መመሪያዎችን በሚገባ ማጥናትና መረዳት
ያስፈልጋል:: ይህም በቆጣሪዎች ለሚነሱ ቆጠራ ነክ ጥያቄዎች ያለማወላወል
ትክክለኛ መልሶችን ለመስጠት ከማስቻሉም በላይ ቆጣሪዎች እምነታቸውን በተቆ
ጣጣሪዎች ላይ እንዲጥሉ ይረዳል::

3. የቆጣሪዎችን አክብሮትና ሙሉ ትብብር ለማግኘት ተቆጣጣሪዎች የራሳቸውን
ክብር የመጠበቅ፣ የቀናነት፣ የአስተዋይነት፣ የታታሪነት፣ የቀጠሮ አክባሪነት፣
ለሥራው ፍጹም ታማኝና ተገዥ የመሆንና የመሳሰሉት ባሕሪያት ማሳየት ይኖር
ባቸዋል::

4. ቆጣሪዎች ልዩ ልዩ ችግሮች /ለምሳሌ መጠለያን፣ ምግብን፣ መጓጓዣን...ወዘተ
የሚመለከቱ/ ሲያጋጥሟቸው ከሕዝባውያን ድርጅቶችና ሌሎች የሚመለከታቸው
አካላት ጋር በመተባበር እንዲፈቱና እንዲሟሉ ማድረግ አለበት::

5. ሊወጣው የማይችል ችግር ሲያጋጥመው የወረዳውን የቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ መጠ
የቅና ማማከር አለበት::

6. በቆጠራው ሥራ በተቆጣጣሪነት ደረጃ የሚሠራ መሆኑን የሚያስረዳ መታወቂያ ስለሚ
ሰጠው ይህንን በማናቸውም ሰዓት ከራሱ ሳይለይ ከማንኛውም ግለሰብ ጋር በሥራ
ጉዳይ ሲገናኝ መታወቂያውን ማሳየት ይኖርበታል:: ይህ ጊዜን ይቆጥባል፣
ለሥራውም ሕጋዊ ድጋፍ ይሰጣል::

7. የቆጠራው ጊዜ አጭር በመሆኑ ቀኑን ሙሉ /ጠዋት እስከ ማታ/ ቅዳሜ፣ እሁድና
ሌሎች በዓላት ጭምር የቆጠራው ሥራ መካሄዱን ማረጋገጥ ይኖርበታል::

8. በተለያዩ ምክንያቶች /ለምሳሌ በሕመም/ ቆጣሪን መተካት በሚመለከት ለወረዳው
የቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በወቅቱ በማሳወቅና በማማከር ማስፈጸም አለበት::

9. ለቆጣሪው የሚያስፈልጉ መጠይቆች፣ ቅጾችና ሌሎች ማቴሪያሎችን ተረክቦ ለቆጣ
ሪዎች ማከፋፈልና እንዲሁም ቆጠራው ከተጠናቀቀ በኋላ መሰብሰብ ያለባቸውን
መጠይቆች፣ ቅጾችና ሌሎች ማቴሪያሎች ከቆጣሪዎች ተረክቦ ማስተላለፍ አለበት::

10. የምዝገባውና የቆጠራው ሥራ በሚካሄድበት ወቅት በተለያዩ ጊዜያት በየደረጃው የሥራ ክንዋኔ ሪፖርት ለወረዳ ቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ያቀርባል።

11. ከሕዝቡ የሚሰበሰቡትን መረጃዎች ተቆጣጣሪውም ሆነ ማንም ቆጣሪ ለሚመለከታቸው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ባለደረቦች ካልሆነ በስተቀር ለሌላ ሰው የተሞሉ መጠይቆችን በማስነበብ፣ በማሳየ ወይም በቃል በመንገር ማስተላለፍ ፈጽሞ የተከለከለ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ መረጃዎችን በሚስጢር መጠበቅ ያለበት ከመሆኑም በላይ በሥሩ ያሉት ቆጣሪዎች ይህን ማድረጋቸውን ማረጋገጥ አለበት።

12. የቆጠራው ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ ቆጣሪዎች ሥራቸውን በሚገባ ማጠናቀቃቸውን በማረጋገጥ ክፍያው እንዲፈጸም አስፈላጊውን ያደርጋል።

<u>የተቆጣጣሪዎች ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት፣</u>

የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የመረጃዎች ስብሰባ ሥራ በተሟላ ሁኔታ እንዲካሄድ ተቆጣጣሪዎች በየደረጃው ማከናወን ያለባቸው ዋና ዋና ተግባራት፣

ሀ. ከዋናው ቆጠራ በፊት የሚከናወኑ ተግባራት
ለ. በዋናው ቆጠራ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት እና
ሐ. ዋና ቆጠራ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚከናወኑ ተግባራት

በተባሉ አርዕስቶች ሥር ተከፋፍለው ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

ሀ. <u>ከቆጠራው በፊት የሚከናወኑ ተግባራት፣</u>

ቆጠራው ከመጀመሩ በፊት የሥልጠና፣ በሚሰጠው ካርታ መሠረት የመቆጣጠሪያና የቆጠራ ቦታዎች የመለየት፣ የቤት፣ የቤተሰብና የድርጅት ምዝገባና ሌሎች ተግባራት ይከናወናሉ። በዚህን ጊዜ ተቆጣጣሪዎች ከዚህ በታች የተመለከቱትና የመሳሰሉት ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሯቸዋል።

1. <u>የተቆጣጣሪዎች ሥልጠና፣</u>

ለተቆጣጣሪዎች በሚሰጠው ሥልጠና በከፍተኛ ደረጃ መሳተፍ አለበት፣

2. <u>በቆጠራዎች ሥልጠና መቢተፍ፣</u>

የቆጠራዎች ሥልጠና በሚሰጥበት ጊዜ በማሠልጠን ተግባር ይበተፋል።

3. <u>ለቆጠራው አገልግሎት የሚውሉ ደኩሜንቶችንና ሌሎች ማተሪያሎችን ከወረዳ ቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ተረክቦ ለቆጣሪዎች ማከፋፈል፣</u> የቆጣሪዎች ሥልጠና ተጠናቅቆ ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች የተመደቡባቸው የቆጠራና የመቆጣጠሪያ በታዎች ወደሚገኙበት ወረዳ ቀና ከተማ ከደረሱ በኋላ እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ለምዝገባውና ለቆጠራው ሥራ የሚያስፈልጉ ደኩሜንቶችንና ሌሎች ማተሪያሎችን ከወረዳው ወይም ከተማ ከሆነ ከከፍተኛ የቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በመረከብ በ" ቆጣሪዎች ከተቆጣሪዎች የቆጠራ ማተሪያሎች የሚረከቡበት ቅጽ /ቅጽ 2/" ውስጥ አየመዘገበ ለእያንዳንዱ በሥሩ ለተመደበ ቆጣሪ መስጠት አለበት። እነዚህ ደኩሜንቶችና ማተሪያሎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ሲሆን ከእያንዳንዱ ዓይነት በአንድ ቆጠራ በታ ውስጥ ያለውን ሥራ ለማስጨረስ የሚበቃ መጠን በቆጠራ ቦርሳ ተደርጎ ለእያንዳንዱ ቆጣሪ መስጠት አለበት።

3.1 የቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች መመዝገቢያ ቅጽ፣
3.2 የሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ — ከተማ /በከተማ ለተመደቡ ቆጣሪዎች ብቻ/
3.3 የሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ — ገጠር /በገጠር ለተመደቡ ቆጣሪዎች ብቻ/
3.4 ተደጋጋሚ ዝብኝት የሚካሄድባቸው ቤተሰብ ኃላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽ
3.5 የቆጣሪ የየቀኑ የሥራ ከንውን መመዝገቢያ ቅጽ
3.6 የቆጠራ በታ ማጠቃለያ ቅጽ
3.7 የቆጣሪዎች መመሪያ /በሥልጠና ጊዜ ለእያንዳንዱ ቆጣሪ የተሰጠ/
3.8 የቆጠራ በታ ካርታ ፋይል /በውስጡ ለካርታ ሥራ የተሞሉ የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጾች፣ የቆጠራ በታ መግለጫና የቆጠራ በታ ካርታን የያዘ/

3.9 አርባስ

3.10 ቀይ ጠመኔ

3.11 ነጭ ጠመኔ

3.12 ልሙጥ ፋይል

3.13 የቆጠራ በርባ /ለሰይ ተዘረዘሩት ደኩሜንቶችና ማተሪያሎች በበርባው ውስጥ በሥርዓት እንደተከ ተቱበት/

3.14 የቆጠራ መታወቂያ

3.15 የትብብር ደብዳቤ

3.16 የቆጠራ ባጅ

ከፍ ብሎ የተጠቀሰው "ቅጽ 2" ም ዕዝል 1 ሆኖ ከዚሀ መመሪያ መጨረሻ ይገኛል።

አያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ደግሞ እንደ አስፈላጊነቱ ለመጠባበቂያና ለቁጥጥር ሥራ ከላይ የተዘረዘሩትንና በተጨማሪም በተለይ ለመቆጣጠሪያ ተግባር የሚከተሉትን ማተሪያሎች በአስፈላጊ መጠን ከወረዳው የቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ተረክቦ መያዝ አለበት።

3.17 የተቆጣጣሪዎች መመሪያ /በሥልጠና ጊዜ የተሰጠው/

3.18 የተቆጣጣሪ የየቀኑ የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ

3.19 የመስክ ሥራ ሪፖር ማቅረቢያ ቅጽ

3.20 የማረካከቢያ ቅጽ

3.21 የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ

3.22 የተቆጣጣሪ መታወቂያ

3.23 የተቆጣጣሪ ባጅ

3.24 የተቆጣጣሪ በርባ /ለሰይ የተዘረዘሩት በውስጡ ተከተው/

## 4. <u>የመቆጣጠሪያና የቆጠራ በታዎችን ለይቶ ማወቅ፣</u>

የመቆጣጠሪያና የቆጠራ በታዎችን ለይቶ የማጥናት ሥራ መሠረታዊና ወሳኝ ጉዳይ እንደመሆኑ ከፍተኛ ትኩረትና ጥናትን ይጠይቃል።

4.1 የቤቶች፣ የቤተሰቦችና የድርጅቶች ምዝገባ ከመጀመሩ
በፊት ተቆጣጣሪው የቆጠራ ቦታና የመቆጣጠሪያ ቦታ
ካርታዎችን በመጠቀም አብረውት ከሚሠሩት ቆጣሪዎች
ጋር በአንድነት የመቆጣጠሪያ ቦታውንና በውስጡ የሚ
ገኙትን የቆጠራ ቦታዎች በማያጠራጥር ሁኔታ በትክክል
ለመለየት ድንበሮቻቸውን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል::
ስለዚህ በየትኛውም አስቸጋሪና ሰዋራ ቦታ የሚገኙትን
ቤቶች በቅድሚያ ማወቅና አቀማመጣቸውን ማጥናት ያስፈ
ልጋል::

4.2 ከአዋሳኝ የመቆጣጠሪያና የቆጠራ ቦታዎች ቆጣሪዎችና
ተቆጣጣሪዎች ጋር በመሆን በካርታዎቹ መሠረት ድንበሮችን ...
4.1 መከለልና ማጥናት ያስፈልጋል:: የካርታው ሥራ ምንም
ቦታ ባይተው ወይም መደራረብ ባይኖርበት እንዲሠራ
ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ቢሆንም በማንኛውም የቆጠራ
ቦታ ካርታ ያልተሸፈነ አነስተኛ ቦታ ቢገኝ ከአዋሳኝ
ተቆጣጣሪ ጋር በመመካከር ከአነስተኛው አዋሳኝ ቆጠራ
ቦታ ተደምሮ ይሰራል:: ትልቅ ከሆነ ግን እንደ
አንድ ቆጠራ ቦታ ራሱን ችሎ ለወረዳው ቆጠራ ጽሕፈት
ቤት ኃሳፊ በማመልከት በሚመደብ ቆጣሪ እንዲሠራ መደ
ረግ አለበት::

4.3 አንድ ትንሽ አካባቢ በመደጋገም በሁለት አዋሳኝ ቆጠራ
ቦታዎች ካርታዎች ውስጥ ከታየ ትልቅ ከሆነው ተሰርዞ
አነስ ካለው ጋር እንዲጠቃለል መደረግ አለበት::

4.4 በካርታ ያልተሸፈኑ ወይም በሁለት ቆጠራ ቦታዎች
ካርታዎች ውስጥ ተደጋግሞ የገባ ቦታ ከተገኘ ስለ
ሁኔታውና ስለተወሰደው እርምጃ በዝርዝር ጽፎ ለወረዳ
ቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃሳፊ ወዲያው ማመልከት ያስፈልጋል::

5. የሕዝብና ቤቶች ቆጠራን ለሕዝቡ ማሳወቅና መቀስቀስ፣

እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ በተመደበበት የመቆጣጠሪያ ቦታ እንደ ደረሰ ከወረዳ የቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊና ከወረዳ የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ኃላፊ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ከከተማ ነዋሪዎች ማኅበርና ከገበሬዎች ማኅበር የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ኮሚቴ አባላት ጋር በመሆን የአካባቢው ሕዝብ በሙሉ ስለ ቆጠራው በሚገባ እንዲያውቅና እንዲተባበር በማሳወቅና በመቀስቀስ ተግባሮች መሳተፍ አለበት፡፡

6. የቤቶች፣ የቤተሰቦችና የድርጅቶች ምዝገባ ማስፈጸም፣

የምዝገባ ሥራ ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች የተመደቡባቸውን ቦታዎችና የአካባቢውን ሕዝብ እንዲሁም ቤቶች የሚገኙበትን አካ-ባቢ ለማወቅ ሲጠቅም ይህም ቆጠራው በተቀላጠፈና በተፋጠነ ሁኔታ እንዲካሄድ ይረዳል፡፡ ስለዚህ ቆጠራውን ለማካሄድ በቅድሚያ በየቆጠራ ቦታ ውስጥ ያሉትን ቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች ለዚሁ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ በቆጣሪዎች ይመዘገባሉ፡፡ ይህን ለማከናወን ተቆጣጣሪዎች የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት መፈጸም አለባቸው፡፡

6.1 ለምዝገባው የቁጥጥር ሥራ የጊዜ ሠንጠረዥ በቅድሚያ ማዘጋጀት፣ የምዝገባውን ሥራ ለማጠናቀቅ ከዋናው የቆጠራ ጽሕፈት ቤት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እያንዳንዱ ቆጣሪ በምዝገባው ጊዜ በሥራ ላይ ቢያንስ ሁለት ጊዜ በመገኘት ለመቆጣጠር የሚያስችል የጊዜ ሠንጠረዥ እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ማዘጋጀት አለበት፡፡ ይህም ሲሆን የምዝገባው ሥራ ተጀምሮ እስከ ሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ ድክመት ለሚታይባቸው ቆጣሪዎች የለጠ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

6.2 ምዝገባውን ለማስጀመር ለቆጣሪዎች መመሪያ መስጠት፣

ቆጣሪዎች የተመደቡበትን የቆጠራ ቦታ ድንበርና በው ስጡ ያሉትን ቤቶች በመዘዋወር በትክክል ለይተው ማወቃቸውን ካረጋገጡ በኋላ ቆጣሪዎችን በሙሉ ሰብስቦ ስለምዝገባው ሥራና ስለተዘጋጀው መጠይቅ አሞላል ላይ ግልጽ ያልሆኑ ነጥቦች ካሉ መነጋገር፣ መወያየትና መመሪያ መስጠት፡፡

6.3 በምዝገባው የቆጣሪዎችን እንቅስቃሴ ማወቅ፣

ቆጣሪዎች የምዝገባውን ሥራ እያከናወኑ ከቤት ቤት በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ የሚሄዱበትን አቅጣጫ በየጊዜው ስጠናቀቀቃቸው ቤተሰቦች እንዲያስውቀ መመሪያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ተቆጣጣሪው ነዋሪዎችን በመጠየቅ ቆጣሪው ያለበትን ቦታና ቤት በቀላሉ እንዲያገኝ ይረዳል፡፡

6.4 ምዝገባውን አስጀምሮ እንዲካሄድ ማድረግ፣

የምዝገባውን ሥራ በ________ ቀን 1976ዓ.ም. ጥዋት አስጀምሮ እንዲካሄድ በማድረግ በተወሰነለት ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ ማድረግ የተቆጣጣሪዎች ኃላፊነት ነው፡፡

6.5 በመጀመሪያ የምዝገባ የቁጥጥር ጉብኝት የሚከናወኑ ተግባራት፣ የቤቶች፣ የቤተሰቦችና የድርጅቶች ምዝገባ ሲጀመር ወዲያው ቆጣሪዎችን በመጎብኘት ሥራውን በዝር ዝር መመርመር፣ ተደጋጋሚ ስሕተቶች ሳይሠሩ ማረምና አስፈላጊ መመሪያዎችን መስጠት ይገባል፡፡ በጉብኝቱ ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች መመርመር ያስፈልጋል፡፡

6.5.1 ቆጠሪዎች የቆጠራ ቦታዎችን ድንበር ምንም ባያባስቱ በውስጣቸው ያሉትንም ቤቶችና ቤተሰቦች ባይዘሉና ባይደጋገሙ የመዘገቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

6.5.2 የቤቶች፣ የቤተሰቦችና የድርጅቶች ምዝገባ ሥርዓት ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ፣

እያንዳንዱ ቆጠሪ በቆጠራ ቦታው ከሰሜንምዕራብ ጫፍ ጀምሮ ወደ ምሥራቅ በማምራት በጥምዝምዝሽ ሁኔታ ሥርዓት ባለው መንገድ ምዝገባውን የሚያከናውን መሆኑን ማረጋገጥ፣

6.5.3 ቆጠሪዎች በተሰጠው የአመዘጋገብ መመሪያ መሠረት መልሶችን በመመዝገቢያው ቅጽ ላይ በትክክል የሞሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

6.5.4 እያንዳንዱ ቆጠሪ በመዘገባቸው ቤቶችና ድርጅቶች በቆጠሪዎች መመሪያ በምዝገባ ጊዜ የቤቶች ተራ ቁጥር አሰጣጥ መመሪያ መሠረት /ሀ/ ገጠር ከሆነ በቤቱ በር ወይም ሌላ አመቺና ሊታይ በሚችል ቦታ ላይ በቀይ ጠመኔ ከ001 በመጀመር ተከታታይ ቁጥር ዬጻፈና /ለ/ ከተማ ከሆነ በከተማው ነዋሪዎች ማኅበር በቤቱ ላይ በተጻፈው ቁጥር አጠገብ በቀይ ጠመኔ የ"×" ምልክት ያደረገ ወይም ቁጥር ያልተሰጠው ቤት ካጋጠመው ደግሞ ቤቱ የሚገኝበትን ትክክለኛ ቦታ ለይቶ በማወቅና ሁኔታውን በማስታወሻ በመመዝገብ ለተቆጣጣሪው ወዲያው የሚያሳውቅ መሆኑን ማረጋገጥ፣

6.5.5 እያንዳንዱ ቆጠሪ ትክክል ጥያቄዎችን በማቅረብ መኖሪያ ቤቶችን፣ መኖሪያ ቤቶችና ድርጅቶችን .. እንዲሁም ድርጅቶችን በትክክል ለመለየት የሚችሉ መሆኑን፣ በተለይ በአንድ መኖሪያ ቤት

ውስጥ ከአንድ ቤተሰብ በላይ የሚኖሩበት ከሆነ እያንዳንዱን ቤተሰብ በትክክል ለይተው የመዘገቡ መሆኑን ማረጋገጥ፤

6.556 የተቆለፉ ቤቶች ወይም መልስ በመስጠት የማይተባበሩ የቤተሰብ ኃላፊዎች ወይም አባላት ቢያጋጥሙዋቸው ወይም መልስ የሚሰጡ የቤተሰብ አባል ባለመኖሩ ምዝገባ ለማካሄድ ባይቻል ቢቀር ቁጠር ከሰጡ በኋላ ቁጠሮውን "ተደጋጋሚ ጉብኝት በሚካሄድባቸው ቤተሰብ ኃላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽ" ላይ ቆጣሪዎች ቁጠሮዎችን የመዘገቡ መሆኑን ማረጋገጥ፤

6.5.7 የመጀመሪያው የቁጥጥር ጉብኝት እንዳበቃ ለወረዳ ቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ከምዝገባው መጀመር በፊት እስከ መጀመሪያው የቁጥጥር ጉብኝት ፍጻሜ ስለነበረው ሥራ ሂደት ሁኔታ ለዚሁ ሥራ በተዘጋጀው "የመስክ ሥራ ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርም" በዝርዝር ሪፖርት ማቅረብ ያስፈልጋል።

6.6 <u>በሁለተኛው የምዝገባ የቁጥጥር ጉብኝት የሚከናወኑ ተግባራት</u>፤ በሁለተኛው ጉብኝት ወቅት በመጀመሪያው ጉብኝት ትኩረት የተሰጠባቸውን ነጥቦች መመርመርና መከታተል ያስፈልጋል። በተጨማሪም የምዝገባው ሥራ ያልተጓተተ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በምዝገባው ሥራ ወደ ኋላ የቀረ ካለ በተፋጠነ ሁኔታ በመሥራት ሥራውን በተመደበለት ጊዜ እንዲያጠናቅቅ ማድረግ አለበት።

6.7 <u>የከተማ ቁጥር የሌላቸውን ቤቶች ተራ ቁጥር ሰጥቶ እንዲመዘገቡ ማድረግ</u>፤ ቆጣሪዎች ባሳወቁት መሠረት በየቀበሌው የከነማ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ የተረጋገጡ ቤቶችን በሚመለከት በቀበሌው የከነማ ቁጥር ያላቸው ቤቶች ምዝ

ገባ እንደተጠናቀቀ ተቆጣጣሪው በቀበሌው ውስጥ ለቤት የተሰጠ ከፍተኛው ቁጥር ምን እንደሆነ ከቀበሌው ከነማ ሽሕፈት ቤት በማጣራትና በውስጥ የሚሠሩትን ቆጣሪዎች አስተባብሮ በማሰማራት ከዚህ ቁጥር ቀጥሎ ከፍ ከሚለው ቁጥር በመጀመር ተከታታይ ቁጥሮች በነዚህ ቤቶች በአመቺ ቦታ ላይ በቀይ ጠመኔ እንዲጻፍባቸውና በቁጥሮቹ አጠገብ የ"×" ምልክት እየተደረገባቸው እንዲመዘገቡ ማድረግ አለበት።

6.8 <u>የተጠናቀቀን የምዝገባ ሥራ ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣</u>

በየቆጠራ ቦታ ምዝገባው ከተጠናቀቀ በኋላ የተሞሉትን የምዝገባ ቅጾች ከእያንዳንዱ ቆጣሪ በመቀበል ቀጥሎ የተመለከቱትን ነጥቦች በሚመለከት በትክክል መሠራታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

6.8.1 የቅጾችና በውስጣቸው ያሉ ዓምዶች ሙሉ በሙሉና በትክክል መሞላታቸውን መመርመርና ማረጋገጥ፣

6.8.2 ወደ ቆጠራ ቦታዎች በመሄድ /ሀ/ በገጠር በእያንዳንዱ ቤት በር ወይም ሌላ አመቺ ቦታ ላይ በማይለቅ ቀይ ጠመኔ የቤቱ ቁጥር ይጻፋል፣ /ለ/ በከተማ በከነማ ወይም በቆጣሪዎች ለቤቱ በተሰጠው ቁጥር አጠገብ በቀይ ጠመኔ የ"×" ምልክት ማድረግ ያስፈልጋል፣

6.8.3 የተዘለሉ ወይም በምዝገባው በትክክልና በተሟላ ሁኔታ ያልተመዘገቡ ቤተሰቦች፣ ቤቶችና ድርጅቶች ከተገኙ የሚመለከታቸው ቆጣሪዎች እንዲመዘገቡዋቸው ማድረግ ነው።

6.8.4 የእያንዳንዱ የቆጠራ ቦታ የቤተሰቦች ዝርዝር ቀደም ሲል የቆጠራ ቦታ ካርታ በተሠራበት ጊዜ ከተመዘገበው የቤተሰቦች ዝርዝር ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ።

ልዩነት ካለ ወይም ስለሁኔታው ምክንያቱን በመግለጽ በጽሑፍ ለወረዳው ቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ማመልከት ያስፈልጋል።

6.8.5 በመጨረሻም የተሠሩ ስህተቶችንና ድክመቶችን በማስታወሻ መያዝ፣ እንዲሁም የምዝገባው ሥራ ተጠናቅቆ ፍጻሜ ላይ መድረሱን "በመስክ ሥራ ሪፖርት ማቅረቢያ ፎርም" ለወረዳው ቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በአስቸኳይ ማሳወቅ ያስፈልጋል።

6.8.6 በምዝገባው ጊዜ የጋርዮሽ መኖሪያ የሆኑ ቤቶች "በጋርዮሽ መኖሪያ ቤቶች መመዝገቢያ ቅጽ" ላይ መመዝገብ ስለሚኖርባቸው መመዝገባቸውን ማረጋገጥ።

6.8.7 መኖሪያ ቤት የሌላቸው ሰዎች የሚያድሩባቸው ቦታዎችም መመዝገብና መጠናት ያለባቸው ስለሆነ በፖሊስ፣ በአብዮት ጥበቃ ጓዶችና በቀበሌ ጽሕፈት ቤቶች ተመራጮች ትብብር በቆጣሪዎች መመዝገባቸው መረጋገጥ አለበት።

ለ. <u>በቆጠራው ጊዜ የሚከናወኑ ተግባሮች</u>፡

የቤቶች፣ የቤተሰቦችና የድርጅቶች ምዝገባ ከተጠናቀቀ በኋላ ቆጠራውን በሚመለከት አያንዳንዱ ተቆጣጣሪ የሚከተሉትን ተግባራት መፈጸም አለበት::

1. <u>ለቆጠራው የሚያገለግሉ ደኩሜንቶችና ሌሎች ማተሪያሎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ</u>፡ ቆጠራው ከመጀመሩ በፊት ባይሟላ የቀረ ወይም የጎደለ መጠይቅ፣ ቅጽ ወይም ሌላ ማተሪያል ካለ ቀደም ብሎ ከወረዳ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ጽሕፈት ቤት ጠይቆ እንዲሟላ ማድረግ ነው::

## 7. የቆጠራ የቁጥጥር ጉብኝት ማድረግ፣

የቆጠራው ሥራ እንደተጀመረ ተቆጣጣሪዎች ተደጋጋሚ የቁጥጥር ጉብኝቶች ማድረግ አለባቸው፡፡ ይኸውም ቆጠራው በተጀመረ ቀን እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ በሥሩ ያሉትን ቆጣሪዎች በሙሉ ጎብኝቶ አሠራራቸውን መቆጣጠር ያለበት ሲሆን ከሁለተኛው ቀን ጀምሮ እስከ ቆጠራው ፍጻሜ ገን እያንዳንዱን ቆጣሪና ቆጠራ ቦታ በሦስት ቀን አንዴ በመጎብኘት ሥራውን በተለያዩ ዘዴዎች በመቆጣጠር ቆጠራው በትክክል መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ በእያንዳንዱ ጉብኝት ጊዜም እያንዳንዱ ቆጣሪ ለሦስት ወይም አራት ቤተሰቦች ቃለ መጠይቆችን እያቀረበ መረጃዎችን ሲሰበስብ ማየትና በተጨማሪም ቢያንስ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ነጥቦች በማሟላት የሚሠራ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

7.1 — ሥነ ሥርዓትና አገባብ ባለው መንገድ ትክክለኛ መልስ ለማግኘት የሚያስችሉ ጥያቄዎች የሚያቀርብ መሆኑን ማረጋገጥ፣

7.2 — የቆጠራ ቦታውን በማያጠራጥር ሁኔታ የሚያውቅና በውስጡ የሚገኙትን ቤቶች ወይም ቤተሰቦች የማይዘል፣ የማይደገም ወይም ከቆጠራ ቦታው ውጭ ስለሆነው ቤት መረጃ የማይሰበስብ መሆኑን፣

7.3 — በቆጠራ ቦታው ውስጥ የሚገኙትን ቤቶችና ቤተሰቦች ሳይዘል ወይም ሳይደገም የሚሸፍን መሆኑን ለማረጋገጥ በምዝገባው የተገኘውን የቤቶችና ቤተሰቦች ዝርዝር የሚጠቀምበት መሆኑን፣

7.4 — የቆጠራው አሠራር ሥርዓት ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ፣

እያንዳንዱ ቆጣሪ በቆጠራ ቦታው ውስጥ ከሰሜን ምዕራብ ጫፍ ጀምሮ ወደ ምሥራቅ በማምራት በጥምዝምዝሽ ሁኔታ ሥርዓት ባለው መንገድ ቆጠራውን ያከናወነ መሆኑን፣

7.5 — ሀ / በገጠር በበሩ ወይም ሌላ አመቺ ቦታ ላይ በቀይ ጠመኔ፣ የቤት ቁጥር ያልተጻፈበትና ወይም /ለ/ በከተማ በከነማ ወይም አንዳንዴም በቆጣሪዎች ለቤቱ በተሰጠው ቁጥር አጠገብ በቀይ ጠመኔ የ"×" ምልክት ያልተደረገበትና በቤትና በቤተሰቦች ዝርዝርም የሌለ ቤት ሲያገኝ በቀበሌው ላሉት ቤቶች ከተሰጡት መለያ ቁጥሮች ከከፍተኛው ቁጥር ቀጥሎ ያለውን ቁጥር በመስጠትና በቁጥሩ አጠገብ በነጭ ጠመኔ የ"×" ምልክት በማድረግ ስለ ቤቱና በቤቱ ውስጥ ስለሚኖሩት ቤተሰቦች መረጃዎች የሚሰበስብ መሆኑን፣

7.6 — በተሟላ ሁኔታ መረጃ ለተሰበሰበላቸው ቤቶች ሀ/ በገጠር በቤቶቹ በር ወይም ሌላ አመቺ ቦታ ቀደም ሲል በቀይ ጠመኔ የቤት ቁጥር በተጻፈበት ቦታ አጠገብ ወይም /ለ/ በከተማ በከነማ ወይም አንዳንዴም በቆጣሪዎች በተሰጠው ቁጥር አጠገብ በነጭ ጠመኔ በደማቁ የ"×" ምልክት የሚደረግ መሆኑን፣

7.7 — ቆጣሪዎች የቆጠሩውን ሥራ ከጀመሩ አንስቶ ያለ አንዳች መጓተት ሥራቸውን የሚያከናውኑ መሆኑን፣

7.8 — የግለሰቦችን ትክክለኛ ዕድሜ ለማወቅ በአካባቢ ታሪካዊ ክንውኖች ዝርዝር ወይም ሠንጠረዥ በሚገባ የሚጠቀም መሆኑን፣

7.9 — የተሞሉ መጠይቆችን በማየትና በመመርመር መሞላት ያለበት ሁሉ ያልተዘለለና በተለያዩ ዓምዶች ውስጥ የሠፈሩት መልሶች እርስ በርሳቸው የሚገናዘቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ለምሳሌ:—

7.9.1 ስለአካባቢ መለያ መረጃዎች በዓምድ 1—11 በትክክል መሞላታቸውን ማረጋገጥ፣

7.9.2 ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የተሞላለት ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና፣ በጾታ፣ ዕድሜና የጋብቻ ሁኔታ የሚገናዘቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

7.9.3 በዓምድ 13 የተመዘገቡትና ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ዝምድናቸው በዓምድ 15 ውስጥ የተገለጸላቸው ልጆች ብዛት በዓምድ 34 ለእያንዳንዱዋ ቤት፡ እቤት ይኖራሉ ከተባሉት ልጆች ብዛት ጋር መመሳከሩን ማረጋገጥ።

7.9.4 ሃይማኖት፣ ብሔረሰብ፣ ቋንቋ፣ የትውልድ ቦታና የአካል ስንኩልነት ሁኔታ-ለሁሉም የቤተሰብ አባ, ላት የተሞላላቸው መሆኑን ማረጋገጥ።

7.9.5 የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል፣ በትምህርት ቤት የመማር ሁኔታ፣ የሥራ ዓይነትና የድርጅቱ ዋና ምርት/አገልግሎት እንደቅደም ተከተላቸው ዕድሜአቸው 5፣ 5 እና 7 ዓመት በላይ ለሆኑ አባላት ብቻ በትክክል መሞላታቸውን ማረጋገጥ።

7.9.6 በዓምድ 34-37 ልደትን በሚመለከት የተሞሉት መረጃዎች ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ሴቶች ብቻ ማረጋገጥ።

7.9.7 ሞትን የሚመለከቱ መረጃዎች በእያንዳንዱ መጠይቅ ላይ መሰብሰቡን ማረጋገጥ።

7.9.8 ስለቤት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በሚመለከት በየዓምዱ ትክክለኛ መልስ በመሆኑ ክብ የተደረገበት ኮዱና በካርዱ ኮለሙ ውስጥ የተጻፈው ቁጥር አንድ መሆኑን ማረጋገጥ።

7.9.9 በአንድ መኖሪያ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ ቤተሰቦች የሚኖሩበት ከሆነ ቤቱን የሚመለከቱ መረጃዎች ከቤተሰቦቹ መካከል ስለአንደኛው ቤተሰብ መረጃዎች በተሰበሰበት መጠይቅ ብቻ መሰብሰባቸውን ማረጋገጥና የመሳሰሉት የማገናዘብ ተግባራት አስፈላጊ ናቸው።

እስከ ሦስት ጊዜ ድረስ መመለስ እንዳለባቸው በመመሪያቸው ውስጥ ተገልጾላቸዋል፡፡ በመሆኑም፦

8.1 ከላይ በተራ ቁጥር 8 የተዘረዘሩትን ቆጠሪዎች የሚያደርጉ መሆናቸውን ተቆጣጣሪዎች ማረጋገጥ አለባቸው።

8.2 ቆጠሪዎች እየተመላለሱ የማይተባበሩ ቤተሰቦችን ለመሸፈን በሚሞክሩበት ጊዜ ተቆጣጣሪዎችም በመተባበር በበኩላቸው ለሚመለከታቸው የቤተሰብ አባላት በማስረዳት፣ በጉረቤት፣ በአካባቢ ሽማግሌ፣ ከዚያም በቀበሌና በገበሬ ማኅበር ተመራጮች በኩል እንዲገለጽላቸው በማድረግ ቆጠሪዎችን መርዳት አለባቸው።

8.3 ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ የማይተባበር የቤተሰብ ኃላፊ ወይም አባል ከተገኘ ግን በአዋጁ መሠረት ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት አስፈላጊውን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

8.4 ሆኖም በቁጥር 8.1– 8.3 መሠረት እንዲተባበር የተደረገ ማንም ግለሰብ ትክክል ያልሆነ መረጃ እንዳይሰጥ አስፈላጊ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሊደረጉ ከሚችሉት ጥንቃቄዎች አንዱ ለተለያዩ ጥያቄዎች የሚሰጣቸው መልሶች እርስ በርሳቸው የሚገናዘቡ ወይም የሚስማሙ መሆናቸው መጠይቁ በሚሞላበት ጊዜ ማረጋገጥ ነው።

9. <u>የአካባቢ ቋንቋ ለማይናገሩ ቆጠሪዎች አስተርጓሚዎች መመደብ</u>።

የተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የሚናገሩ ቆጠሪዎችን ተገቢው የቋንቋ ክልል ውስጥ በመመደብ ቋንቋን በሚመለከት ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ችግሮች ለመወጣት ጥረት ያደርጋል፡፡ ሆኖም አንዳንድ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ቆጠሪዎች በተፈለገው መጠን ለመመልመልና መመደብ ባለመቻሉና በአንዳንድ የቆጠራ ቦታዎች የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪ ብሔረሰቦች አባላት የሆኑ

ሰዓት ጀምሮ እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ በሥሩ የሚገኙትን ቆጣሪዎች በማሰማራትና በመቆጣጠር መኖሪያ ቤት የሌላቸው ሰዎች የሚያድሩባቸው በቦታዎች ድረስ በመሄድ በፖሊስ ሠራዊት አባላት፣ በአብዮት ጥበቃ ጓድ አባላትና በቀበሌ ተመራጮች ትብብርና እርዳታ እስኪነጋ ድረስ እንዳይበታተኑ በማድረግ፣ ተገቢ ገለጻ በማድረግና በመገባባት በተዘጋጀው "የሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ" ላይ ስለነሱ የተለያዩ መረጃዎች እንዲሰበሰቡ ማድረግ አለበት።

## ሰ. ቆጠራው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚከናወኑ ተግባሮች፣

1. እያንዳንዱ ቆጣሪ የቆጠራውን ሥራ እንደፈጸመ መረጃዎች ያልተሰበሰበለት ወይም በከፊል ብቻ የተሰበሰበለት ቤተሰብ ወይም አባል እንዳይኖር ተደጋጋሚ ጉብኝት የሚካሄድባቸው ቤተሰብ ኃላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽና ሌሎች ቅጾችን በጥንቃቄ እንዲመረመርና ከተሞሉት መጠይቆች ጋር እንዲያገናዝብ መመሪያ መስጠትና ይህንን ማድረጉን መቆጣጠር ያስፈልጋል። ያልተሸፈነ ወይም በከፊል መረጃ የተሰበሰበለት ቤተሰብ ወይም አባል ካለ በአስቸኳይ እንዲጠናቀቅ ማድረግ እና እንደዚሁም የሞላቸውን መጠይቆች አንድ በአንድ በማየት በትክክል መሞላታቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ ይገባል።

2. ተቆጣጣሪዎች የተሞሉት መጠይቆች በቤቶችና ቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ ውስጥ ካለው ዝርዝር ጋር ሙሉ በሙሉ የሚገናዘቡ መሆኑን በማስተያየት አንድም ቤት ወይም ቤተሰብ ያልተዘለለ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። ያልተሸፈኑ ቤቶች ወይም ቤተሰቦች መኖራቸው ከተረጋገጠ የሚመለከታቸው ቆጣሪዎች ቤቶች ወይም ቤተሰቦቹ ድረስ ተመልሰው በመሄድ መረጃዎች እንዲሰበሰቡላቸው ማድረግ ይገባል።

3. ተቆጣጣሪው የተሞሉና ያልተሞሉ መጠይቆችንና ሌሎች ማተሪያሎችን ከእያንዳንዱ ቆጣሪ በሥርዓት ሲረከብ ተቆጣጣሪውና ቆጣሪዎች ከመቆጣጠሪያ ቦታው ከመልቀቃቸው በፊት የተሞሉ መጠይቆችን ከዳር እስከ ዳር በማንበብ በተለያዩ ዓምዶች ውስጥ የተሞሉ መልሶች እርስ በርሳቸው የሚገናዘቡ መሆናቸውን መርምሮ በማረጋገጥ በትክክል የተሠሩ መሆናቸውን በሚገባ ማረጋገጥ አለበት:: ስህተት ያለባቸው ወይም በተሟላ ሁኔታ ያልተሞሉ መጠይቆች ከተገኙ እን አስፈላጊነቱ የሚመለከታቸው ቆጣሪዎች ወደ ቆጠራ ቦታቸው ተመልሰው የሚመለከታቸውን ቤተሰቦች ወይም አባላት ፈልገው በማግኘት መጠይቆችን የተሟሉ እንዲያደርጉ ወይም እንዲያስተካክሉ ወይም እንደገና አዲስ መጠይቆችን እንዲሞሉ ማድረግ አለበት:: መጠይቆችና ቅጾች በትክክል መሞላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ብቻ ቆጣሪዎች የየራሳቸውን የተሞሉና ያልተሞሉ መጠይቆች፣ ቅጾችና ሌሎችም ማተሪያሎች ይዘው አብረውት ወደ ወረዳው ቆጠራ ጽሕፈት ቤት እንዲሄዱ በማድረግ ወረዳው ከደረሱ በኋላ የተሞሉና ያልተሞሉ መጠይቆችና ሌሎች ማተሪያሎችን በተዘጋጀው "ተቆጣጣሪዎች ከቆጣሪዎች የቆጠራ ማተሪያሎች መረከቢያ ቅጽ" ላይ መዝግቦ ከእያንዳንዱ ቆጣሪ መቀበል አለበት:: ይህ ቅጽ /ቅጽ 3/ በዚህ መመሪያ መጨረሻ ላይ ዕዝል 2 ሆኖ ገብቶአል::

4. በቆጣሪዎች "በቆጠራ ቦታ የቆጠራ ውጤት ማጠቃለያ ቅጽ" ላይ የተጠቃለሉት መረጃዎች ቆጣሪዎች የተጠቃለሉባቸውን ቅጾች በመለዋወጥ የአንዱን ሌላው አይቶ በትክክል መጠቃለሉን እንዲያረጋግጡ ካደረገና እራሱም አይቶ በትክክል መሠራቱን ካረጋገጠ በኋላ መቀበልና በመቆጣጠሪያ ቦታው ውስጥ ያሉት ቆጠራ ቦታዎች "በመቆጣጠሪያ ቦታ የቆጠራ ውጤት ማጠቃለያ ቅጽ" ላይ አጠቃሎ ሁለቱን ቅጾች ለወረዳ የቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወዲያውኑ መላክ፣ እነዚህ ቅጾች ዕዝል 3 እና 4 ሆነው በዚህ መመሪያ መጨረሻ ይገኛሉ::

5. በመጨረሻም እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ከእያንዳንዱ ቆጣሪ የተረከባቸውንና በእጁ ያሉትን የተሞሉ መጠይቆች፣ ሌሎች ዶኩሜንቶችና ማተሪያሎች በፋይል በፋይል ውስጥ ሆነው ብዛታቸውም ከውጭ በየፋይሉ ላይ ተጽፎ በቆጣሪው በርሳ ውስጥ በሥርዓት

የገቡ ወይም የተከተቱ መሆናቸውን ከረጋገጠ በኋላ ለዚሁ የተዘጋጁትን "የተጠናቀቁ ፎርሞች መረካከቢያ ቅጽ /ቅጽ 4/" እና "ከተቆጣጣሪ እስከ ዋናው ጽሕፈት ቤት የቆጠራ ማቴሪያሎች መረካከቢያ ቅጽ /ቅጽ___/"

በመጠቀም ለወረዳው የቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ማስረከብ አለበት። የሚያስረክበው ዶኩሜንቶችና ማቴሪያሎችም ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው፡-

5.1 የቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች መመዝገቢያ ቅጾች /የተሞሉና ያልተሞሉ ለየ ብቻ/።

5.2 የሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቆች — ገጠር /የተሞሉና ያልተሞሉ ለየ ብቻ/።

5.3 የሕዝብና የመኖሪያ ቤቶች ቆጠራ መጠይቆች — ከተማ /የተሞሉና ያልተሞሉ ለየብቻ/።

5.4 የቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጾች /መረጃዎች የተጠቃለሉባቸው/።

5.5 ተደጋጋሚ ጉብኝት የሚካሄድባቸው ቤተሰብ ኃላፊዎች መመዝገቢያ ቅጾች /የተሞሉ/።

5.6 የቆጣሪ የየቀኑ የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጾች /የተሞሉ/።

5.7 የቆጠራ ቦታ ካርታ ፋይሎች /ለያንዳንዱ ፋይል በውስጡ ለካርታ ሥራ የተሞሉ የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ፣ የቆጠራ ቦታ መግለጫና የቆጠራ ቦታ ካርታን የያዘ/

5.8 የቆጣሪ መታወቂያዎች፣

5.9 የትብብር ደብዳቤዎች፣

5.10 የቆጣሪ ባጅ

5.11 የቆጣሪ ቦርሳዎች /በእያንዳንዱ ውስጥ ከአንዱ ቆጣሪ የተሰበሰቡት ከላይ የተዘረዘሩት ማቴሪያሎች

በሥርዓት ተከትተው / እንዲሁም ተቆጣጣሪው በቀጥታ ከራሱ የሚከተሉትን በራሱ በርሳ ውስጥ አድርጎ ማስረከብ አለበት፡—

5.12 የመስከ ሥራ ሪፖርር ማቅረቢያ ቅጽ /የተሞላ /

5.13 የመቆጣጠሪያ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ /የተሞላ /

5.14 የተቆጣጣሪ የየቀኑ የሥራ ከንውን መመዝገቢያ ቅጽ /የተሞላ /

5.15 የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ

5.16 የተቆጣጣሪ መታወቂያ

5.17 የተቆጣጣሪ ባጅ

5.18 የተቆጣጣሪ በርሳ /በ5.12.—5.17 የተዘረዘሩት ሁሉ በውስጡ በሥርዓት ተቀምጠው/

ተቆጣጣሪው የተሞሉ መጠይቆችንና ቅጾችን ስምና ብዛታቸው "ያተጠናቀቁ ፎርሞች መረካከቢያ ቅጽ" እንደዚሁም የሌሎች የቆጠራ ኩሜንቶችንና ማተሪያሎችን ስምና ብዛት "ከተቆጣጣሪ እስከ ዋናው ጽሕፈት ቤት የቆጠራ ማተሪያሎች መረካከቢያ ቅጽ /ቅጽ__" በተባሉት ቅጾች ውስጥ በሁለት በሁለት ኮፒ በሥርዓት ከመዘገበ በኋላ የአስረካቢና የተረካቢ ስም፣ ማዕረግና ፊርማ እንደዚሁም ቀን በማስፈር ርክክቡ ይከናወናል፡፡ መረካከቢያ ቅጾቹም እንደ ደረሰኝ በማገልገል አንዱ ኮፒ ለወረዳው ቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሲሆን ሁለተኛው ለተቆጣጣሪው ይሆናል፡፡ የእነዚህ ቅጾች ዓይነት ዕዝል 5 እና ዕዝል 6 ሆነው በዚህ መመሪያ መጨረሻ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ከላይ የተዘረዘሩትን መጠይቆችና ሌሎች የቆጠራ ማተሪያሎች ለወረዳው የቆጠራ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በሚያስረክብበት ጊዜ ማቴሪያሎቹን በሥርዓት በአንድነት ማሠር(pack) አለበት፡፡ ይህም ሲሆን የመቆጣጠሪያ ቦታው የሚገኝበትን ክፍለ ሀገር፣ አውራጃና ወረዳ ስም በጉልህ በአንድ ወረቀት ላይ ጽፎ በአንድ በኩል ከውጭ በግልጽ ለማየት በሚችል ሁኔታ ከመጠይቆችና ሌሎች የቆጠራ ማተሪያሎች ጋር ማሰር አለበት፡፡ ተቆጣጣሪዎች ከላይ የተዘረዘሩትን መጠይቆች፣ ቅጾችና ሌሎች የቆጠራ ማተሪያሎች በሚገባ በማስረከብ ደረሰኝ ሳይቀበሉ አበላቸውን ማግኘት አይችሉም፡፡

በተጨማሪም ተቆጣጣሪው የእንደዚህ ዓይነቱን ቆጣሪ ሥራ በጥብቅ መቆጣጠር አለበት፡፡

2. አንዳንድ ቆጣሪዎች በቆጠራ ሥራ ባለቸው ኃላፊነት የተነሳ በድፍረት ገንዘብ ወይም የመሳሰሉ ጥቅሞችን በመጠየቅና በማስገደድ ከነዋሪዎች ለማግኘት ይሞክሩ ይሆናል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት የተጠረጠረና የተረጋገጠበት ቆጣሪም ከዚህ በላይ በቁጥር 1.2 በተገለጸው ሁኔታ እንዲሠራ ይደረጋል፡፡

3. አንዳንድ ቆጣሪዎች ከቆጠራ ሥራቸው በተጨማሪ አንዳንድ ዕቃዎችን ከከተማ ወደ ገጠር በመውሰድ መሸጥና መለወጥን ተግባር ላይ እና በመሳሰሉት ተግባሮች ላይ ይሰማሩ ይሆናል፡፡ ይህም የቆጠራውን ሥራ ፈጽሞ የሚያደናቅፍ፣ የሚያሰናክልና የሚጎትት ጉዳይ ስለሆነ እንዲህ የሚያደርጉትንም ቆጣሪዎች ከፍ ብሎ በቁጥር 1.2 በተገለጸው መሠረት የቆጠራውን ሥራ እንዲያከናውን ያደርጋል፡፡

4. አንዳንድ ቆጣሪዎች በቆጠራው ሥራ በሚሳተፉበት ወቅት መልካም ሥነ ምግባር የጎደለው ባሕርይ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ይህም ፈጽሞ መሆን የማይገባው ስህተት ስለሆነ እንደዚህ ዓይነት ባሕሪይ ያሳየውን ቆጣሪ መምከርና ማስጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

እነዚህንና ሌሎች የመሳሰሉትን ድክመቶች በእንጭጩ ለመቅጨትና ለማስተካከል የሚቻለው ገና የቆጠራው ሥራ ከተጀመረበት ዕለት ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ ሳይታክቱ ጥበብና ትጋት በተሞላበት ንቃት፣ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ ብቻ ነው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን ጥፋቶች በተደጋጋሚ የፈጸመ ቆጣሪ ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ቆጠራው እንደተጠናቀቀ አስፈላጊውን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

# የ1976 ዓ.ም የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ　　　ቅጽ 8

## ተቆጣጣሪ ለወረዳ ቆጠራ ጽ/ቤት ኋላፊ የቆጠራ ዶክመንቶችና ማቴሪያሎች ማስረከቢያ ቅጽ

1. ክፍለ ሀገር ______ 2. አውራጃ ______ 3. ወረዳ ______

4. የገበሬ ማኅበራት ብዛት ______ 5. በከተማ ከሆነ የከተማው ስም ______

6. ክፍተኛ ______ 7. የመቆጣጠሪያ ቦታ መለያ ቁጥር ______

8. የቀበሌዎች ብዛት ______ 9. የቆጠራ ቦታዎች ብዛት ______

| ተራ ቁጥር | | የዶክመንቶችና ማቴሪያሎች | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | | መጠሪያ (አርዕስት) | ብዛት | |
| | | ሀ) መጠይቆችና ቅጾች | | |
| 0 | 1 | የቤቶች፣ ቤተሰቦችና ድርጅቶች መመዝገቢያ (ቅጽ—1) | | |
| 0 | 2 | የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ጥራዞች —— ገጠር | | |
| 0 | 3 | የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ጥራዞች —— ከተማ | | |
| 0 | 4 | የቆጠራ ውጤት ማጠቃለያ ቅጽ (ቅጽ—4) | | |
| 0 | 5 | ተደጋጋሚ ጉብኝት የሚካሔድባቸው ቤተሰብ ኋላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽ (ቅጽ—2) | | |
| 0 | 6 | የቆጣሪ ዕለታዊ የሥራ ክንውን መመዝገቢያ (ቅጽ—3) | | |
| 0 | 7 | የተቆጣጣሪ ዕለታዊ የሥራ ክንውን መመዝገቢያ (ቅጽ—5) | | |
| 0 | 8 | | | |
| | | ለ) ካርታ | | |
| 0 | 9 | የቆጠራ ቦታ ካርታ | | |
| 1 | 0 | የቆጠራ ቦታ መግለጫ | | |
| 1 | 1 | የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ | | |
| 1 | 2 | | | |
| | | ሐ) ሌሎች | | |
| 1 | 3 | ቦርሳ | | |
| 1 | 4 | ባጅ | | |
| 1 | 5 | መታወቂያ | | |
| 1 | 6 | | | |
| 1 | 7 | | | |
| 1 | 8 | | | |

| | ስም | ማዕረግ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|---|
| አስረካቢ | | | | |
| ተረካቢ | | | | |

## የ1976 ዓ.ም የሕዝብና የቤቶች ቆጠራ　　　ቅጽ 9

**ከወረዳ ቆጠራ ጽ/ቤት እስከ ብሔራዊ ቆጠራ ጽ/ቤት የቆጠራ ዶኩሜንቶችና ማቴሪያሎች መረካከቢያ ቅጽ**

1.ክፍለ ሀገር ________ 2.አውራጃ ________ 3.ወረዳ ________

4.በአስተዳደሩ ውስጥ ያሉ ከተሞች ብዛት ________ 5.የከፍተኛ ብዛት ________

6.የቀበሌዎት ብዛት ________ 7.የገበሬ ማሕበራት ብዛት ________

8.የመቆጣጠሪያ ቦታዎች ብዛት ________ 9. የቆጠራ ቦታዎች ብዛት ________

| ተራ ቁጥር | | የዶኩመንቶችና ማቴሪያሎች መጠሪያ (አርዕስት) | | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| | | ሀ. መጠይቆችና ቅጾች | | |
| 0 | 1 | የቤቶች፣የቤተሰቦችና የድርጅቶች መመዝገቢያ (ቅጽ-1 ) | | |
| 0 | 2 | የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ጥራዞች — ገጠር | | |
| 0 | 3 | የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ መጠይቅ ጥራዞች — ከተማ | | |
| 0 | 4 | የቆጠራ ቦታ ማጠቃለያ ቅጽ (ቅጽ—4) | | |
| 0 | 5 | ተደጋጋሚ ጉብኝት የሚደርግባቸው ቤተሰብ ኋላፊዎች መመዝገቢያ ቅጽ (ቅጽ-2 ) | | |
| 0 | 6 | የቆጣሪ ዕለታዊ የስራ ክንውን መመዝገቢያ (ቅጽ-3 ) | | |
| 0 | 7 | የተቆጣጣሪ ዕለታዊ የስራ ክንውን መመዝገቢያ (ቅጽ-5 ) | | |
| 0 | 8 | | | |
| | | ለ. ካርታ | | |
| 0 | 9 | የቆጠራ ቦታ ካርታ | | |
| 1 | 0 | የቆጠራ ቦታ መግለጫ | | |
| 1 | 1 | የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ | | |
| 1 | 2 | የወረዳ ካርታ | | |
| | | ሐ. ሌሎች | | |
| 1 | 3 | ቦርሳ | | |
| 1 | 4 | ባጅ | | |
| 1 | 5 | መታወቂያ | | |
| 1 | 6 | | | |
| | | | | |
| | | | | |

| | ስም | ማዕረግ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|---|
| አስረካቢ | | | | |
| ተረካቢ | | | | |

ውስጥ የሚካሄደው የቆጠራ ሥራ አራተኛው ዙር የቁጥጥር ዝግጅት በተጠናቀቀበት ጊዜ ካለቀ አራተኛው የመሥክ ሥራ ሪፖርት የመጨረሻው ይሆናል::

7 / በመጨረሻም አምስተኛውን ዙር የቁጥጥር ዝግጅት እንዳጠናቀቀና የቆጠራው ሥራ እንደተፈጸመ ከዚህ በላይ በቁጥር /6 / የተጠቀሰውን የቅጽ–10 ክፍል በትክክል በመሙላት የመጨረሻውን ሪፖርት ያቀርባል::